# እስከመቼ ኢትዮጵያ!

የማይነጥፈው የኢትዮጵያ ማህፀን፤
ከዓመት ዓመት፣ ከገዢ ገዢ
ካምባገነን አምባገነን፤
ሳይደክም ሳያርፍ የሚጎርፈው፣
ሚሊዮን ሃያ ሁለት አፍርቶ ነበር በትውልዴ እኔ ሳውቀው።

**አሁንማ፣ አሁንማ፣**
ካራት እጥፍ በላይ አድጓል አሉኝ፤
ደስታ በፊቴ ሲረጩልኝ።

የማይደክመው መቃብር በበኩሉ፤
ቀን ነው መሽቷል
ሳይል አፉን ከፍቶ በጥቅሉ፤
ያጋፈዋል ልጆቿን በሙሉ።

**እስኪ ተጠየቅ ታሪክ!**
**እስኪ እንጠየቅ እኛ!**
አስከመቼ ኢትዮጵያ!
የስቃይ የዕልቂት መናኸሪያ!

ይህ በቂም በቀል ተረግዞ፣
ሀገርን በመጥላት ተመርዞ፤
አንዱን ወገን በሌላው ወገን ማባላቱን
ሙያዬ ብሎ ይዞ፤

የሀገራችን ሕልውና
ለሥልጣኑ መደላድል፣
አድርጎ መሰላል፤ መቀመጫ ደልዞ፤
አማራውን ማጥፋት
የሕልውናው ምሰሶ
ያደረገ ቡድን፤

አኙዋኩን፣ አሮሞውን፣ አጋዴኑን፣
ደቡቡን፣ ሰሜኑን፣ ምሥራቁን፣ ምዕራቡን፤
መሐከሉን እና ዳሩን
በየተራ በየተራ፣
ወደ ጥፋት እያመራ፤
አንዱን ገድሎ
አብሮ አልቅሶ፣
ሕዝብን ቀብሮ
አሳንሶ፤
ለመቃብር ወይ ለስደት፣
ለመንጋ ረሃብ ወይ ለጦር እልቂት፤
ያገሬን ሰው፣
አንዱን ካንዱ ሲደራርት፤
ምን ይባላል!
ምን ይታያል!
በአእምሮስ ውስጥ
ምን ይሰላል!
**ይግረማችሁ ወገኔ!**
ራሱ የሳለው ጎራዴ፤
ያነገበው ጦር አነሰና!
ለጎረቤት ገዳዮች
በሩን በርግዶ ከፈተና!
አስጨረሳቸው
ይህ አረመኔ ሀገር ሻጭ ይሄውና!
ምን አለች ያቺ እናት፣
የልጇ ሞት ሲነግሯት?
ምን አለ አባታለም፣
እንግዲህ ባብዩ ሚለው የለም

# ኢትዮጵያ ሀገሬ



ልጅን አጥቷል ለዘላለም።

እስኪ ንገሩኝ?
እንዴት ነው ሀገር ሀገር የሚኮነው፣
በሳት ረመጥ የሚኬደው?
የት ላይ ሆኖ ነው የሚለቀሰው፣
በገፍ ግፍ ወርዶ ሕዝብ ሲጨንቀው?
እስኪ ንገሩኝ የምታውቁ፣
በወገን ማለቅ ‘ምትጨነቁ?
ማነው እዬዬ የሚልላት?
በሜዲትራኒያን ባህር ጥልቀት፣
ዕይኖቿ ሲጨነቁ፣
ከንፈሮቿ ሲደርቁ?
እንዴትስ በልተን እናድራለን፣
ወገናችን በረሃብ ሲያልቅ እየሰማን?
ያገር ያለህ አይባል
ሀገር ያለውን ታውቃላችሁ፤
የወገን ያለህ አይባል
ወገን ተሰዶ፣
እኛም ተሰደን፣
ታያላችሁ።
ኸረ ለመሆኑ መቼ ነው፤
ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የምትሆነው?
እስከመቼ ኢትዮጵያዬ!
እስከመቼ ወገኔ!
የምሰማው ታሰረች እሷ፣
አብሮ ታሰረ ጥንስሷ።
የምሰማው ተሰደደ፣
ሀገር አቋርጦ ሄደ።

የምስማው አለቁ፣
        በባህር ውስጥ ወደቁ።
በሌላ ሀገር እግር ብረት፣
        አጠለቁ።
የምስማው ሆነ ያገር መሐሉ ዳር፣
        ለሙ መሬት ሲሸጥ ማደር።
ኧረ ልባችሁን መርምሩ!
        ዙሪያችንን እንመልከት!
                ጥቁር ለብሰን፣
                እንባ ተራጭተን፣
                ልባችን ከፍተን፣
                ምርር ብለን
                        አብረን ማልቀሱን ቻልንበት።
እስኪ ማልቀሱን ሙያ ብለን አንያዘው
        በደል መዘርዘሩን ትግል አንበለው
አንድ ሁለት ብለን ሟች መቁጠሩ
        አይሁንብን የዕለት ተግባሩ
ለቅሷችንም ልክ ይኑረው
        አጥር ሠርተን እንከልለው
                እናብሰው! እናድርቀው፣ እንለውጠው፣
እንዳይደገም  ቃል እንግባ፣!
        ከንግዲህ ወዲህ እንዳናነባ!
                አስለቃሻችንን ያልቅስ ያንባ!

**እንወቅበት!  እንወቅበት!  እንወቅበት!**

አንዱዓለም ተፈራ

ማክሰኞ፤ ሚያዝያ ፲፰ ቀን፤ ፳፻፰ ዓመተ ምህረት ( 4/26/2016 )

ረቡዕ፤ ሚያዝያ ፲፱ ቀን፤ ፳፻፰ ዓምተ ምህረት በሳን ሆዜ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለሚሰበሰቡ ኢትዮጵያዊያን የተነበበ